የጀነት ሰዎች ጀነት የገቡ ጊዜ አላህ ተባረከ ወተዓላ እንዲህ ይላል "አንዳች ነገር እንድጨምርላችሁ ትፈልጋላችሁን?

ከሱሀይብ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ
ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: «የጀነት ሰዎች ጀነት የገቡ ጊዜ አላህ ተባረከ ወተዓላ እንዲህ ይላል
"አንዳች ነገር እንድጨምርላችሁ ትፈልጋላችሁን?" እነርሱም "ፊታችንን አላበራህልንምን? ጀነት አስገብተህስ ከእሳት
አላዳንከንምን?" ይላሉ። ነቢዩ እንዲህ አሉ "የፊቱን ግርዶሽ ይገልጣል። ወደ ጌታቸው ዐዘ ወጀል ከመመልከት የበለጠ ተወዳጅ የሆነ አንዳችም ነገር አልተሰጣቸውም።"»
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የጀነት ሰዎች ጀነት የገቡ ጊዜ አላህ ተባረከ ወተዓላ ለነርሱ እንዲህ እንደሚል ተናገሩ: እንድጨምርላችሁ የምትፈልጉት አንዳች ነገር አለን? ሁሉም የጀነት ሰዎችም እንዲህ ይላሉ: ፊታችንን አላበራኸውምን? ጀነት አስገብተህስ ከእሳት አላዳንከንምን? አላህም ግርዶሹን አስወግዶ ይገልጠዋል። የፊቱ ግርዶሽም ብርሃን ነው። ወደ ጌታቸው ዐዘ ወጀል ከመመልከት የበለጠ ተወዳጅ ነገርም አይሰጣቸውም።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/8344